# የይኩኖ አምላክ ልጆች፣ ንስር አሞራውና በረራ 710

ያሬድ ጥበቡ

ማርች 24፣ 2007

ለስዊዘርላንድ የቅንጅት ድጋፍ አባላት ስብሰባ የቀረበ

ከትናንት በስቲያ አንድ ወዳጄ የብሪቲሽ ላይብረሪን ወይም ወመዘክርን ላስጎብኝህ ብሎ ወሰደኝና፣ በመስታዎት ሳንዱቅ ውስጥ ተቆልፈው ለታይታ ከተዘረጉት ያለፈው ሚሌኒየም መባቻና መጀመሪያ ላይ ከተፃፉት የብራናና የእንጨት፣ የፓፒረስና ወረቀት የሃይማኖቶች ድርሳኖችና መፅሃፈ ቅዱሳን መሃል በይኩኖ አምላክ ዘመን (በ1262 ላይ) የተጠረዘው የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስ ምንጮችን (ቢብሊዮግራፊ) ያካተተ ባለ ብዙ ገፅ የብራና ስንክሳር ለማየት ተቻለን ። የዕድል ነገር ሆኖ፣ ሌሎቹን ቀልቤን የሳቡ የሩቅ ዘመን መዛግብት በፊልም ቀርጬ ሳስቀር ያላተኮረችብኝ ዘብ፣ የኢትዮጵያው ጋ ስደርስ ኡኡታዋን ስላቀለጠችው በካሜራዬ ሳልከትበው ቀረሁ ። ሆኖም የቻልኩትን ያህል በዐይነ ህሊናዬ አክስዬ ለማቆየት ያደረግሁትን ጥረት ባካፍላችሁ ይህን ይመስላል ።

ያ የብራና መዝገብ የተከፈተው ቀይ ፈርጦች ጣል ጣል የተደረገበት ነጭ ካባ ያጠለቀው የአቡዬ ተክለ ሃይማኖት ወዳጅ አፄ ይኩኖ አምላክ ተቀምጦ የሚያሳይ ሲሆን፣ ከበስተጀርባው አንጋቾቹ ከግራው ደግሞ እጅ ለመንሳት የመጡ የአረቢያ አምባሳደሮች በግመል ላይ ተቀምጠው፣ ለንጉሱ ያላቸውን ከበሬታና ፍርሃት የሚያንፀባርቅ ገፅታ አጥልተው ይታያሉ ። ከወገባቸውም በላይ ራቁታቸውን ናቸው ። ኢትዮጵያውያኑ አንጋቾች ገፅ ላይ ደግሞ የሚታየው የግስላ ነብር አዳኝ ገፅታ፣ አረባውያኑ ላይ ከሚነበበው ፍርሃትና ከበሬታ ፣ ንጉሱ ገፅ ላይ ከሚነበበው ደግነትና ኩራት ጋር፣ አእምሮዬ ከአንዱ ወደሌላው እየተመላለሰ በነበረችኝ ጥቂት ደቂቃ ውስጥ በአግራሞት ተውጬ ደነዘዝኩ ። እንዲሁ በዝምታ ከቤተመዘክሩ አሜሪካ ኤምባሲ ፊት ለፊት ወደሚደረገው የቅንጅት ደጋፊዎች የተቃውሞ ሰልፍ የሚወስደውን የሎንዶን ቀይ ባስ ይዤ ሄድኩ ።

የይኩኖ አምላክ ደግነትና ኩራት፣ የአንጋቾቹ ግስላና ነብርነት፣ በዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ በህዋሳቸው የከሰለውን የእመ ኢትዮጵያ እንባ የሚያነቡና፣ ድምፃቸውን ለታፈኑ በማዋስ « ጆርጅ ቡሽ መንግስታት ያልፋሉ፣ አንተም ታልፋለህ፣ የመለስም አሰቃቂ አገዛዝ ያልፋል፣ የኢትዮጵያ ህዝብና ታሪክ ግን ዘላቂ ናቸው፣ የዛሬ ዝምታህም ከጭካኔ ባልተለየ መንገድ በታሪክ ይፈረጃል» የሚለው ድምፃቸው ከሩቅ ያስተጋባል ። የክረምቱ ቆፈንና ብርድ የሚቻል አልነበረም ። ሆኖም የሰው ሰብአዊ ክህሎት ይሄው ነው ። ለማረግ ወደሚፈልገው ሰማይ ከመድረስ የሚያግደው ሃይል ያለመኖሩ ። የማየትና ማለም አቅሙ ብቻ ነው፣ ወደ አርያም መወንጨፊያ ክንፉን ሰብረው፣ የእኩዮች መጫወቻ የሚያደርጉት ።

ከሰልፈኞቹ ፊት ለፊት  ከኤምባሲው አናት ላይ የአሜሪካ ሰንደቅ አለ ። ከሰንደቁ ስር የህንፃው ግንባር ላይ ወደል ግልገል አንሳ አሞራ ክንፉን ዘርግቶ ቁለቁል ደካሞችን ሊሞጨልፍ አኮብኩቦ ይታያል ። ከመሬቱ ላይ የይኩኖ አምላክ የልጅ ልጆች ለቅሶአቸውንና ዋይታቸውን ያሰማሉ ። ለሰሚ የሚያሳዝን ተማፅኖአቸውን ያስተጋባሉ ። ከኢትዮጵያውያን ሠልፈኞቹ በስተቀኝ ወገቡን በሁለት እጆቹ የያዘ የጦር መኮንን  ሃውልት ቆሟል ። ከሃውልቱ ፊት የእንግሊዝ ፖሊሶች ቆመው ያወራሉ ።  ግልገል አንሳውና መኮንኑ የኢትዮጵያውያኑ ጩኸት የገደዳቸው አይመስልም ። ሙያ በልብ ነው ያሉ ይመስላል ። ከቶ ምን ይሻለን ይሆን ? ጩኸታችንና ዋይታችንን የሚሰማ ጠፍቶ፣ ይባስ ብሎም «እርባና ያለው ተቃውሞ ሰለሌለ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተደላድለዋልና  የእርዳታ እጃችሁን ዘርጉ» የሚል እዝና ማባበያ ለአውሮፓውያኑ እየተላለፈ መሆኑንና፣ ይህንንም መልእክት የሚያስተላልፈው ሌላ ሳይሆን ጥንት በንስርነት ራሱን ያጨውና ወደ አርያም ለማሻቀብ ክንፉን ዘርግቶ የነበረው፣ ዛሬ ግልገል አንሳነት መርጦ ደካማና ጨቅላ ለመመንተፍ ቁልቁል ወደመሬት የሚመለከት መሆኑ የአጋጣሚ አይመስለኝም ።

ትናንት በማለዳ የብሪታኒያን አየር መንገድ ይዤ ወደዚህ ስብሰባ ለመምጣት ከለንደን ወደ ዙሪክ በረራ 710 ላይ እያለሁ፣ «ሃይ ላይፍ» የተሰኘውን መፅሄት ሳገላብጥ «ፌየር ጌም» የተሰኘ መጣጥፍ ላይ ቀልቤ አረፈ ። ይዘቱም፣ ኪነት ባሁኑ ዘመን በሃራጅ መሸጡ ቀርቶ፣ ለንደን፣ ፓሪስ፣ ንው ዮርክ፣ ዱባይ ወይም ማስትሪክት ውስጥ በአመት አንዴ በሚዘጋጁ ፌየርስ ወይም ዘመናዊ ጉልቶች ላይ የሚሸጡ መሆናቸውንና፣ ይህም ተጨማሪ ሃገር ጎብኚዎችን ለመሳብ ስለሚያደርገውና ስላደረገው አስተዋፅኦ የሚተነትን ነው ። ከአለም የኪነት ውጤቶች 50 በመቶ የሚሆኑት በነዚህ መሰል ጉልቶች ላይ የሚሸጡ መሆናቸውንም ድርሰቱ ያብራራል ። አንዱ ጉልት በሌላው ላይ የበላይነት ለመያዝም፣ ለአብነት ኮሎኝ የማስትሪክት ታናሽ ወንድም ተደርጎ መታየት ስለሰለቸው፣ የጉልቱን ገበያ ወር ከሚያዚያ ወደ መጋቢት ያስቀደመ መሆኑን ዘግቧል ።

ይህ የአውሮፓውያኑ የሥነ ኪነት ጉልቶች ውድድር ዜና የመሰጠኝ ያለምክንያት አልነበረም ። በዘር ማጥፋት ወንጀል በሃሰት የተከሰሰው ከንቲባችን ተመሳሳይ ህልም እንደነበረው አውቅ ስለነበር ብርሃኑን ስላስታወሰኝ ይመስለኛል ። ከንቲባ ብርሃኑ ነጋ የፊንፊኔን አንድ ክፍል ለይቶ የአፍሪካ የሥነ ኪነት መንደር ለመቆርቆር ታላቅ ህልም ነበረው ። መኪናዎች ከሩቅ ቆመው፣ ለእግረኛ ብቻ በተሰሩ ትላልቅ አደባባዮች መሃል ህፃናት ከወላጆቻቸው ጋር የሚዝናኑበት፣ ለቱሪስት መስህብ የሚሆን የአፍሪካ የሥነ ኪነት ማዕከል ለመፍጠር ይመኝ ነበር ። ቢያድለን ኖሮ በአጭር አመታት ውስጥ ከላይ በመፅሄቱ ከተዘረዘሩት የኪነ ጥበባት ጉልቶች ተርታ አዲስ አበባችንም ልትደመር ትችል እንደነበር በመቆጨትም ነበር መጣጥፉን ያጣጣምኩት ። ያውም በአመት የአንድ ወር ጉልት ብቻ ሳይሆን፣ በየወሩ የሁለት ሶስት አፍሪካ ሃገሮችን የጥበብ ውጤት እያሳየች፣ 13 ወራትን በጥበብ ያጌጠች መዲና ትሆን ነበር ።

የከንቲባ ብርሃኑ የአፍሪካ ኪነት መንደር እውን ቢሆን፣ አዲስ ቀፎ እንደተሠራለት ንብ ሁሉ፣ የአፍሪካ ቀዳማይት እመቤት የሆነችውን ንግስት ፍለጋ፣ የየሃገሩ ሠአሊና ከያኒ ንቦች ሁሉ «ክተት» ብለው፣ የፖለቲካ መዲናነቷን የተቀበሏትን አዲስ አበቤ፣ የባህል መዲናቸውም ሊያደርጓት እርሳስ ክርታሳቸውን ሰንቀው፣ የቻለ ባየር፣ ያልቻለ እግሩ እስኪነቃ በመኳተን፣ አንድ ትልቅ አፍሪካዊ የኪነት መንደር እንደሚፈጥሩ ሃቅ ነበር ። ሆኖም ይህን የከንቲባችንን ምኞት ለመግደል የወየኑ የፅልመት ሃይሎች በፈፀሙት ክህደት፣ ከሰኔ 97 እስከ ጥቅምት 98 ባወረዱት ግፍና ብካይ አፍሪካዊው የሥነ ኪነት ሊቃውንት ወደ ፊንፊኔ መምጣታቸው ቀርቶ፣ በዘመኑ የአስረኛ ክፍል ምሩቅነታቸው ዲፕሎማ የተናኛቸው ኢትዮጵያዊ ወጣቶች፣ አጋዚያዊ ስድቡ፣ ውርደቱና፣ ዱላው ይባስ ብሎም ረሃቡና ግርፋቱ አስመርሮአቸው፣ ከፊሉ ሳሃራ በረሃን ለማቋረጥ፣ ከፊሉ ነጭ አባይን ለመሻገር ሲጥር፣ ሃሩርና የውሃ ጥም፣ ውሃ ሙላትና አዞ ሲል እያደረገውና እየቀረጠፈው፣ ካሰበበት ሳይደርስ፣ ድሃ ወላጆቹም የደህንነቱን ወሬ እየተጠባበቁ፣ መርዶ ነጋሪ እንኳ ጠፍቶ ደጅ ደጁን እያዩ ተቀምጠዋል ።

በዚህ ሁሉ ብካይ ማግስት፣ በሰኔና ጥቅምት ግድያ እንዲደረግ ያዘዙት ጠቅላይ ሚኒስትር ግን ከግንቦት 97 በፊት ወደር የለሽ ዴሞክራሲያዊ ምርጫና ነጭ ካፒታሊዝምን እመሰርታለሁ ብለው በፈከሩበት አፋቸው፣ ዛሬ ከሃገራቸውም አልፈው ላፍሪካ የሚያስፈልጋት «እድገት ተኮር መንግስት እንጂ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አይደለም» በሚል የተሸናፊ ዲስኩር የፈረደበትን ካድሬአቸውን በማደንቆር ላይ ናቸው ። አሁን ማ ይሙት በምርጫ ላይ ያጡትን ህጋዊነት፣ በዲስኩር መአትና በኢኮኖሚ እድገት ሊያገኙ ይቻላቸዋልን? ፈፅሞ ። የማይሞከር ነው ። ኢትዮጵያ ሲንጋፖር አለመሆኗን ሩቅ ሳይሄዱ ከናታቸው ባድማ ወይም ወጀድ መማር ነበረባቸው ። ፈጣሪው በልቦናው ያጫረውን የነፃነት መንፈስ ገድሎ፣ በቀን 22 ሳንቲም የነበረች ጉርሱን 43 አደርግልሃለሁና ተንበርክከህ ተገዛ የሚለው የአቶ መለስ ተማፅኖ፣ በሥልጣን የታወረ አእምሮ የሚፈብርከው ባዶ ጨኸት እንጂ፣ ለእናት ኢትዮጵያ ራእይ የሚመጥን መልስ አይደለም ። ትክክለኛው መልስ፣ ከንቲባው በውስጣዊ የመንፈስ ሃይሉ አምጦ የወለዳትን ትልሙን፣ በወረቀት ላይ ነድፎ፣ በምድር ላይ ምሶ የሚገነባበትን ነፃነት ሳይውሉ ሳያድሩ እውን ማድረግ ነው ። «ይህ ርዕይ እንዴት እውን ሊሆን ይችላል?» ብላችሁ የምትጠየቁ አያሌ እንደሆናችሁ ይረዳኛል ።

አራት አንኳር ሃሳቦችን ላካፍላችሁ ። በመጀመሪያ ትልቁ መሳሪያ የይኩኖ አምላክን ቅም አያቶች ውቃቢ መለመን ነው ። ከመለመንም በፊት ከነዚህ የሥልጣኔ አንጋፎች እግር ሥር ተቀምጦ፣ ሀ ሁ ወይም አቡጊዳ መቁጠር ነው ። ይህ አይነቱ ኢትዮጵያዊ ስብስብ በየሚኖርበት መንደር፣ እንደየንደኝነቱ፣ እንደየ እውቀት ደረጃው፣ እየተሰባሰበ፣ ኢትዮጵያዊ የመፅሃፍ ክበቦችን ማቋቋምና፣ ራሱን ለማወቅና ሃገሩን ለመረዳት ጥረት ማድረግ መተኪያ የማይገኝለት ተግባር ይመስለኛል ። የመጀመሪያ መልእክቴ ራሳችንን እንወቅ ነው ። እናጥና እንመርምር ነው ። ልቦናችንን እንክፈት ነው ። በምርምርና በመመሰጥ ያላገኘናቸውን «እውቀቶች» በይደር እናስቀምጣቸው ነው ። አበክረን ወደውስጣችን ተመልክተን፣ ደክመን ባገኘናቸው እውነቶች የድንቁርናና የማን አለብኝ ስሜታዊነታችንን እንተካ ነው ። አንድ በሉ ።

ሁለተኛው፣ ዘመናዊነትን የተቋደሱ ህዝቦች ምን ቢያደርጉ ከዚያ ደረሱ፣ ምንስ ብናደርግ ከዚህ መቀመቅ ገባን ብለን ሌላ የጥናት ዘርፍ መክፈት ነው ። ራሳችንን ለመጥላት ሳይሆን፣ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን አስጎብድደን አውሮፓዊ ለማድረግም ሳይሆን፣ አስቀድመን ባጠናነውና በምርምር በደረስንበት የራሳችን ማንነት ላይ ተመሥርተን እንደ ሌሎቹ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሃብት ለማካበት ያጋጠሙንን ችግሮች፣ የተዘናጋንበትን ምክንያት ለመፈተሽ ነው ። ለምን መሪዎች መፍጠር አቃተን? አንድ ጎበዝ ብቅ ሲል አናት አናቱን ቀጥቅጠን እራሱን የምናሰደፋው ለምን ይሆን? ጎበዙስ ለምን ቶሎ ራሱን ይደፋል? እውን በባሃላችን ያለው «አስቀድሞ የደረሰ የማሽላ እሸት የወፍ እራት ይሆናል» የሚለው ብሂል ምን ያህል ስርጎን ገብቶ፣ የፈጠራ ችሎታችንን ሊያዳፍነው በቃ? ተከባብረንና ተፋቅረን ተነቃቅፈንና ተቻችለን የጋራ የሆኑ ተቋማትን መፍጠርና፣ ኮትኩተን ማሳደግ ለምን ተሳነን? ከጎናችን የነበሩም ሆኑ (እነ ሞሮኮ)፣ ከኋላችን የነበሩ እንዴት አስከነዱን? እነርሱ ምን ሲያደርጉ እኛ ምን እያደረግን ነበር? ሁለተኛው ምክሬም

ጥናት ነው ። ለዚህ መሰሉ ጥናት መሳለጥ ያግዝ ይሆናል በሚል ውጥንም ነው፣ «መወያየት መልካም» የሚል ፕሮግራምም በ«ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ኔትወርክ» ላይ ለማዘጋጀት የምደክመው ።

በሶስተኛ ደረጃ፣ አብረውን የሚያሰሩና ልቦናችንን የሚከፍቱ፣ ክፋታችንንና ምቀኝነታችንን የሚያኮሱ ስነ ምግባሮችን ፈልፍለን ማወቅ ይመስለኛል ። እነዚህ የርስ በርስ ግንኙነታችንን በማስለጥ፣ ለህግጋት የተገዛን፣ ከስም ማጥፋትና መረን ከለቀቀ ግለኝነትና አጉል ዝና በመጠበቅ፣ ለሥራ እንድንተጋና፣ በትጋት የሚሠሩትንም የሚገባቸውን ፍቅርና ከበሬታ እንድንሰጥ በማግባባት ወደ አርያም ለመመንጠቅ፣ መስፈንጠሪያ ማማ ሆነው የሚያገለግሉንን መሰረታውያን መለየት ነው ። ወደዚህ ወደአውሮፓ ያመጣኝ አንድ የጥናት ስብሰባ ላይ፣ ይህን በሚመለከት ሌንጮ ለታ ተጨንቆ ተጠቦ የጨመቀው መመሪያ ይጠቅም ይሆናልና ላካፍላችሁ፣ እንዲህ ይላል፣

1 - ለተወለድንበት ቤተሰብም ሆነ ብሄረሰብ እንዲሁም ሃይማኖትም ሆነ አካባቢ ቋንቋም ሆነ የጎረቤቶቻችን ማንነት በምርጫና በውዴታችን የመጣ እንዳልሆነ እንረዳ፣
2 - ሆኖም ከአመፅና ጦርነት የፀዳ የጋራ የፖለቲካ ሥርአት ለማቆም ምርጫ እንዳለን እንገንዘብ
3 - የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ከማጥላላትና ለመደምሰስ ከመመኘት ይልቅ በግልፅና በቅንነት ልናወያያቸው እንሞክር
4 - ተቃዋሚዎቻችንና በሃሳብ የሚለዩን ሁሉ ከኛ ያላነሰ የሞራል ብቃትና ሃላፊነት እንዳላቸው እንገምት
5 - ዕሴቶቻችንና እምነቶቻችን ፍፁምና የማይገሰሱ አድርገን ከማየት ይልቅ ሊታረሙና ሊሻሻሉ እንደሚችሉ እንመን
6 - ከታሪክ የወረስነውንም ሆነ የዛሬውን የፖለቲካ ሥርአት ፍፁም ከማወደስም ሆነ ፍፁም ከማይሰይጠን ተቆጥበን፣ ሊጎለብቱ የሚገባቸው መልካም ጎኖችና ሊወረወሩ የሚገባቸው ድክመቶች እንዳሉዋቸው እናሰላስል የሚሉ ይገኙባቸዋል ። የኦቦ ሌንጮን ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ ባንደግፍ እንኳ በአብዛኛው ከተስማማን፣ የፖለቲካ ክርክራችንና ውይይታችን ዘመናዊ ቅርፅ እንዲይዝ ይረዳናል ብዬ አስባለሁ ።

በአራተኛ ደረጃ በሃሩር የምንጠበስበት፣ በብርድ የምንቆላበት፣ ለቅሶ ዋይታችንን የምናሰማበት የኢትዮጵያ ጉዳይና የመሪዎቻችን ደህንነትና ነፃነት ትግል ያስገኘውን ውጤትና፣ ያጋጠሙትን ችግሮች መመርመር ማጥናትና መፍትሄ መፈለግ ነው ። ሃያላኑ ለምንድን ነው የማይሰሙን? ንስር አሞራው ወደ ግልገል አንሳነት እንዴትና ለምን ተለወጠ? በመድረክ በሚያሰማው ዲስኩርና፣ በተግባር በሚፈፅመው ክፋት መሃል፣ የሚያደርስብንን እመቃ ለማሳነስ ምን ብናደርግ ይሻላል? ግንቦት 97 በኢትዮጵያ የፖለቲካ አውድማ ላይ ያስነሳውን የነፃነት ጥማት የሚመጥን ሥራ እንሥራ ከተባለ፣ በየዋህነትና በማንብደድ ሊከናወን ሲችል አይታየኝም ። ስለ ግልገል-አንሳው መንግስታዊ አሠራር፣ የጥቁር የእኩልነት ትግሎችን ለማዳፈን ስላደረጋቸው ሰርጎ ገብ ሥራዎችና «ኮ ኢንቴል ፕሮ» ስለተሰኘው የ ኤፍ.ቢ.አይ ፕሮግራም፣ አሻንጉሊት መንግስታቱን ለመደገፍ ሊሄድ የሚችልባቸውን ርቀቶች ማጤን፣ መረዳትና፣ መከላከያ ማዘጋጀትም ይገባ ይመስለኛል ።

የጦር መኮንኖች በብዛት በሚከዱበትና በሚታሰሩበት፣ ህሊና ያላቸው ዳኞች ሃገር ጥለው በሚሰደዱበትና፣ ለ193 ዜጎች መገደል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠያቂ መሆናቸውን የሚገልፀ የአጣሪው ኮሚሽን አባላት ተአማኒ ሰነድ ይዘው እግራቸው ኬንያ አምስተርዳምና ለንደን በደረሰበት ቅፅበት፣ የቅንጅት አለም አቀፍ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ድንገት በዕለተ ሰንበት ማለዳ ተነስተው፣ «አለም አቀፍ ኮሚቴ የሚባለው ማወናበጃ ነው፣ እኔ እገሌንም አባርሬአለሁ» ማለታቸው የአጋጣሚ ከሆነ፣ ዕውነትም ሃገራችን የተአምራት ሃገር መሆኗን ከመቀበል ሌላ ምንስ ማለት ይቻለኛል? ሊቀመንበሩም ይህን ሲወስኑ ብቻቸውን እንዳልሆነ የታወቀ ነው ። ከኋላቸው ሃይ ሓይ የሚሉዋቸው ፣ በተሞከረው የስደት ድርጅት ውስጥ ሁሉ እየገቡ፣ ዱክትርናቸውንና ኢንጂኔር ስማቸውን እንደ ፈቃድ ወረቀት የሚጠቀሙበትንና፣ ከስም ማጥፋትና ማተራመስ በቀር፣ በሚያምኑበት ወግ አጥባቂነታቸውም ሆነ በሚምሉበት የኢትዮጵያም ሆነ የአማራ ብሄርተኝነታቸው ያደራጁትና ያንቀሳቀሱት ሃይል ወይም ድርጅት አለመኖር የሚመሰክረው ነገር ቢኖር፣ የብአር ኩሊ ተልእኮአቸው ለግንባታ ሳይሆን ለጥፋት መሆኑን ነው ። የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ለወግ አጥባቂ ርዕዮትም ቢሆን በቂ ቦታ ስላለው፣ በእምነታቸው ዙሪያ ማሰባሰብና ማደራጀቱን ባስቀደሙ ነበር:: አላማቸው ያ ስላልሆነ ግን፣ በተግባር ላይ ተሰልፈው አይገኙም ። አለበለዚያማ ከ16 አመታት በፊት የወያኔን የሽግግር መንግስት በመርዳት ለአንድ አመት ተኩል በክልል 14 ፀሃፊነት በመስራቱ፣ «ለአንድ አመት ተኩልም ቢሆን፣ ከሚገባው በላይ ቆይቻለሁና ይቅርታ አድርጉልኝ» ብሎ በመድረክም ሆነ በመፅሃፍ የጠየቀን ታጋይ ለማጥፋት ቀን ከሌት መባዘናቸው በለመዱት የአሉባልታ ተልእኮ የኢትዮጵያን ድርጅቶች የማዳከምና የማፈራረስ ተግባር ሌላ ምንም እርባና እንደሌላቸው ምስክር ይመስለኛል ።

ወደ ራሳችን ልመለስና፣ ሌላው ልናጤነው የሚገባ ነገር፣ የምንማጠናቸውን ሃይሎች ማንነት ማጥናትና፣ የተማፅኖአችንን ቃላት ከማስተካከል ጀምሮ፣ በዚህ መሰል ልመና ሊገኝ የሚችለውን ውጤት ዳራና ወሰን መለየት፣ ተስፋ መቁረጥ እንዳይመጣ መከላከያ የብረት ቆባችን ይመስለኛል :: በእብሪት መዶሻ ራስ ራሳችንን እንዳይቀጠቅጡን :: አዲስ የትግል ስልቶችን ማፈላለግ፣ በየምንኖርባቸው ከተሞች፣ ባለሥልጣናቱን ከመማጠን አልፈን፣ ነዋሪው ህዝብ የኢትዮጵያን ሃቅ እንዲረዳ፣ የመሪዎቻችን እንግልት እንዲሰማው፣ የኢትዮጵያን የነፃነት ተስፋ እንዲደግፍ፣ የተለያዩ ስልቶችን ቀይሰን መድከም ይኖርብናል :: ይሄኛው ውጤቱ ቶሎ የማይታይ ሊሆን ይችላል፣ ግን ዘላቂ ነው :: ይቻላልም :: ይህንንም ለማወቅ ሩቅ መሄድ የለብንም፣ ኤርትራውያን በ17 አመታት ትግላቸውን ለአለም ለማሳወቅ የተጠቀሙባቸውን መንገዶችና ያገኙዋቸውን ድጋፍና ሃዘኔታ ማጥናት ነው :: እነርሱ ካደረጉት፣ ሊቀለን ካልሆነ፣ ሊከብደን የሚችልበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም :: እንዲህ አይነት ተግባር ውስጥ ለመሳተፍ ግን ትግሉ ረጅም መሆኑንና፣ ዋናው የትግል አውድማ ሃገር ቤት መሆኑን ለአፍታም ልንረሳው አይገባም :: ይህን መሰል መዘናጋት ውስጥ የገባን እለት አልቆልናል ማለት ማጋነን አይመስለኝም ::

ዋናው የትግል አውድማ ሃገር ቤት ነው ሲባል፣ የውጪው ሥራ ሃያላንን በመማለድና ገንዘብ በማዋጣት የታገደ ነው የሚለው አመለካከት አዘናጊና ትግሉን የሚጎዳ ይመስለኛል :: በድጋፍ ሥራ ውስጥ የመሪነት ችሎታቸውን ያዳበሩት፣ የኢትዮጵያን ታሪክና ለመዘመን ያገጠሚትን ጋሬጣዎች የመረመሩ፣ ያጠኑና ከፍተኛ ንቃተ ህሊና ያዳበሩ፣ በህሊናቸው ሃይል የነፃነትና መብት ጥማት ያቃጠላቸው፣ ከጥማታቸው ጋር የሚመጥን የትግል መስክ ውስጥ ይገቡ ዘንድ፣ የፓርቲው አመራር ሁኔታዎችን የማመቻቸትና፣ የተለያዩ የአባልነት ደረጃዎችን ፈጥሮ፣ ትግሉ የሚያስፈልገውን ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ ይጠበቅበታል :: እስካሁን ይህን ለማድረግ ለምን አልተቻለም?

ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ይታዩኛል :: የመጀመሪያው ከላይ የጠቀስኩት በውጪ የሚኖረው ዜጋ የሚታይበት ውሱንነት ነው :: ለብዙዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከሃገሩ ተሰዶና ለምዶ በውጪ ሃገራት የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ፣ እንደሚታለብ ላም ከማየት ያለፈ ግምት ያለ አይመስለኝም:: ይህ በጣም የተሳሳተ ግንዛቤ ነው :: ባለፉት የ33 አመታት ልምዳችን እንኳ ብንወሰን (ለጊዜው የርእዮተ አለምን ጉዳይ ወደጎን ትተን)፣ የየካቲት ንቅናቄ እንደተጀመረም ሆነ ከመጀመሩ በፊት ራሳቸውን ለትግል አጭተው፣ ሊያስከትል የሚችለውንም መስዋእትነት ተቀብለው ከአውሮፓና አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ከተሞችም ሆነ ወደ ትጥቅ ትግሉ አውድማ ያመሩ ሃገርና ህዝብ ወዳድ ዜጎች ጥቂት አልነበሩም :: ከነዚህም ውስጥ ዶክተሮች፣ ኢንጂነሮች፣ ኢኮኖሚስቶች በብዛት ይገኝ -ባቸው ነበር :: ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ዶክተር ሃይሌ ፊዳ፣ ዶክተር ንግስት አዳነ፣ ነጋ አየለ፣ ወይዘሮ ፍቅርተ ወዘተ በከተማው ትግል፣ እነ ማህሙድ ማህፉዝ፣ ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ እነ አብዲሳ የአፋር በረሃን አቋርጠው ትግራይ ገጠር የገቡት የውጪ ኑሮን ትተውና ላመኑበት ለመሰዋት ቆርጠው እንደነበር ስናስታውስ፣ የነዚህ ጀግኖች ታናናሽ እህቶችና ወንድሞች ከገንዘብ ማዋጣት ድጋፍ የበለጠ፣ ለሃገራቸው የሚፈይዱት የለም የሚለው አስተያየት የዋህ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ስድብም ሊቆጠር የሚገባው ይመስለኛል ::

ሁለተኛው ችግር፣ በአለም አቀፍ አመራሩ በኩል የሚታየው ሌሎችን ያለማሳተፍና፣ አመራሩን በማስፋት የትግሉን አድማስ ማስፋት ሥራ በይደር የተወው መሆኑ ነው :: «መሪዎቻችን እስኪፈቱ ድረስ ውክልና ሰጥተውናል እንጂ፣ ድጋፍ ስራውን ከማስተባበር የዘለለ፣ ሙሉ የፓርቲ አመራር እንድናደርግ አይጠበቅብንም» በሚመስል እምነት፣ የፓርቲ ሥራውን እግር ተወርች አስረው ተቀምጠዋል የሚል እምነት አለኝ :: የድጋፉ ተግባር ዴሞክራሲያዊ በሆነ መሠረት ላይ እየተገነባ፣ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ አመራር ወደ መስጠት የሚሸጋገርበት ወቅት እየተቃረበ ሰለሚመጣ፣ ኪል የተሰኘው አካል፣ የድጋፍ ስራውን ማስተባበር ዋነኛ ተልእኮው አለመሆኑን ተረድቶ፣ ለተመሠረተበት የፓርቲ ሥራን የማገዝ ሃላፊነት በተገቢው ለመወጣት መነሳሳት ይጠበቅበታል :: በስምንት፣ ጊዜም ሆነ አቅም በሌላቸው ሰዎች የፓርቲ ስራውን አፍኖ፣ ከንፈር እየመጠጡ፣ አንድ ሰው በሚሰራው የሥነ ፅሁፍና የድርጅት ስራ ላይ ብቻ ተሞካሽቶ መቀጠል ወንጀል ነው :: እንደምታዘበው፣ ሻንጣ ይዞ ከሃገር ሃገር መዘዋወርና፣ አብዛኛውን ሰአት በኤየር ፖርቶችና ሆቴሎች ማሳለፍ እንደ ትግል የሚቆጠርበትና፣ ይህንንም ቀጠና (**turf**) ከሌሎች ለመከላከል፣ «አላስገባም በሩን፣ የጌታዬን» የማለት የነቀዝ አስተያየት እየደነደነ እንዳይሄድ ነቅቶ መጠበቅና፣ ለውጥ እንዲኖር ማስገደድ፣ በደጋፊዎች ላይ የወደቀ ተግባር እየሆነ የመጣ ይመስለኛ ል ::

ለማጠቃለልም፣ በመግቢያዬ በጀመርኳቸው ሶስት ገጠመኞች ልፈፅም :: የብሪታኒያ ወመዘክር የይኩኖ አምላክ ማህደር፣ በዱሮው ንስር አሞራ፣ በዛሬው ግልገል አንሳ አሞራ እግር ስር

ለኢትዮጵያ የሚያነቡት ልጆቿ ጨኸትና፣ የበረራ 710 የኪነ ጥበብ ጉልት ያጫረው የአዲስ አበባችን ጭንጋፍ ተስፋ የተቆራኙ ክስተቶች ይመስሉኛል ። ያለ ይኩኖ አምላክ ኩራትና ደግነት ከዚህም የምንከተበው ሃቅ ከሌለ፣ ለነፃነትና መብት የምንጮህበት ትናጋ ይዘጋል ። ኢትዮጵያን ከአውሮፓውያኑ እኩል ለማዘበን እንቅልፍ የማይተኛ ህሊናና ርዕይ ሲኖረን ብቻም ነው የይኩኖ አምላክ ኩራትና ደግነት ላይ መድረስ የሚቻለን ። የዚህም ስብሰባችን ፋይዳ በነዚህ ኩነቶች መሃል ያለውን ትስስር ለመፈተሽና፣ ምን ሆነን እዚህ ደረስን? ንስር አሞራውንስ ሽቅብ ወደ አርያም ከመመንጠቅ ይልቅ፣ ቁልቁል ወደ መሬት ደካሞችን ወደ መመንተፍ እንዲወርድ ምን አስገደደው? ከበረራ 710 የኪነ ጥበብ ጉልት የማይተናነስ አፍሪካዊ የሥነ ጥበብ መንደር ለመመሥረት ርዕይ የነበራቸውን መሪዎቻችንስ የስቃይ ቀን እንዴት እናሳጥረው ብለን ለመመካከር ብንጠቀምበት ተገቢ ይመስለኛል ። በመጨረሻም፣ ከታሪካችን እንማር፣ ከቅን አያቶቻችን በወረስነው ማንነታችን እንኩራ፣ እንወቃቸው፣ እንመርምራቸው፣ አዲስ እውቀትም ከገበየን፣ ያልተመረመረ የስማ በለው «መረጃችንን» አሽቀንጥረን ለመወርወር ድፍረቱ ይኑረን ። እናጥና፣ እናጥና፣ ሰልሰን እናጥና

ምናልባት ለማሳረጊያ ሰሞኑን የተረጎምኳትን አንድ የአፍሪካ ህዝብ መዝሙር ስንኝ ልቋጥርና በዚያው ልሰናበታችሁ ። እንዲህ ይላል ፣

| | |
|---|---|
| Lift every voice and sing | ሰማይና መሬት እስኪደም |
| Till earth and heaven ring, | ለነፃነት ማህሌት እስኪቆም |
| Ring with the harmonies of Liberty; | ፍንደቃችን አየሩን ይሙላው |
| Let our rejoicing rise | የሚያደምጡት ጠፈራት እስኪደርስ |
| High as the listening skies, | እንደ ባህራቱ ማእበል እየተመመ |
| Let it resound loud as the rolling sea. | ከውድቀታችን ጨለማ የከተበውን ሃቅ እያዜመ |
| Sing a song, full of the faith that the dark past has taught us, | ዛሬ ያመጣውን ተስፋ ሰንቆ እያስገመገመ |
| Sing a song, full of the hope that the present has brought us. | የአዲሱን ቀን ጅማሮ ያበሰረችውን ፀሃይ ይዘን |
| Facing the rising sun of our new day begun, | እስከ መጨረሻው ድል ይቀጥል ሰልፋችን |
| Let us march on till victory is won. | ሁሉም ድምፁን ያሰማ ይዘምር |
| | |
| Stony the road we trod, | የምንጓዝበት መንገድ እሾሃማነት |
| Bitter the chast'ning rod, | የምንገረፍበት ጉማሬ መራራነት |
| Felt in the days when hope unborn had died; | ተስፋ ባላረገዝንበት ዘመን የነበረን ስቃይ ሞቷል |
| Yet with a steady beat, | ግርፋቱ ቢቀጥልም |
| Have not our weary feet | ከአባት እናቶቻችን ተስፋ መሬት፣ |
| Come to the place for which our **mothers/fathers** sighed? | እግሮቻችን ሳይደርሱ አይዴደክሙም |
| We have come, over a way that with tears has been watered, | በእንባ በራሱ መንገዶች ላይ ተራምደን |
| We have come, treading our path through the blood of the slaughtered. | በታረዱት ደም በጨቀየው ጎዳና ላይ |
| Out from the gloomy past, | ተጉዘን |
| Till now we stand at last | ከጭጋጉ ጨለማው ርቀን፣ ዛሬ በመጨረሻ የቆምነው |
| Where the white gleam of our bright star is cast. | የተስፋችን አብሪ ኮከብ ከምታበራበት ፀዳል ነው |
| | |
| God of our weary years, | የጭንቀታችን ደራሽ አምላክ |
| God of our silent tears, | የዝምታ እንባችን አባሽ፣ የውስጥ ለቅሷችን ደራሽ |
| Thou who has brought us thus far on the way; | ጉዟችንን ከዚህ አድርሰህ |
| Thou who has by thy might | በውስጣችን ባሰረፅከው ብርሃን እየመራህ |
| Led us into the light. | |
| Keep us forever in the path we pray, | ጉዞአችንን እንድንቀጥል ፅናቱን እንድትሰጠን |
| Lest our feet stray from the places, our God, where we met thee, | አንተን ካገኘንበት ጎዳና እንዳንወጣ |
| Lest our hearts, drunk with the wine of the world, we forget thee, | በአለም ከንቱ ወይን ሰክረን ልባችን እንዳይደክም |
| Shadowed beneath thy hand, | በእጆችህ ሥር ጠልለን |
| May we forever stand | ፅናት ስጠን አዝልቀን |
| True to our God | በልባችን ለለኮስከው ነፃነት |
| True to our native land. | ለእመ-ሃገራችን ፍቅር እስከ ወዲያኛው እንድንቆም |